ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

**Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)**

http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974

ጋዜጣዊ መግለጫ

ኪል-008/07
የካቲት 22 ቀን፣1999 ዓ.ም

# በእብሪት ፍትህን እየፈነገጡ ከታሪክ ተጠያቂነት ማምለጥ አይቻልም

የካቲት 26 1999 ኢ.ም. የወያኔ የፖለቲካ ችሎት እራሱን የዳኝነትና የፍትህ ለምድ አልብሶ በሃሰት በወነጀላቸው የቅንጅት መሪዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ተሚጋቾች ላይ ብይን ለማሳለፍ ይሰየማል:: ህዝብ የሚጠብቀው ይህንን ነው:: ነገር ግን ይህ ሁላችንም የምንጠብቀው የፍርድ ሂደት እንደማይከናወን ከአሁኑ ታውቋል:: የሚቀጥለው ሰኞ የካቲት 26 የሚያስችለው ፍርድ ቤት ምን መወሰን እንደሚገባው እንደተለመደው በመለስ ዜናዊና በግብረአበሮቹ ተመክሮበት ያለቀለትን የትእዛዝ ውሳኔ ተቀብሏል:: ይህ ውሳኔ ፍርድ ቤቱ ሌላ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቶ የህሊና እስረኞቹን በእስር እንዲቆዩ የሚያድረግ ነው::

ይህ የወያኔ/ኢህአዴግ ውሳኔ ግን ቀድሞ ከምናውቀውና ወያኔ የሃገሪቱን ፍትህ ስርአት በማንተት የቂምና የበቀል ፍላጎቱን ለማርካት ሲወስዳቸው ከነበሩት ውሳኔዎች ለየት የሚያደርገው ነገር አለ:: እንደሚታወቀው የውሳኔው አንዱ ገጽታ ንጹሃንን ማሰቃየት ቢሆንም ሌላው ገጽታ በቅርቡ የራሱ የህግ አማካሪዎች ከሰጡት ቀጥተኛ ምክር ጋር የተያያዘ ነው:: ወያኔ/ኢህአዴግ ያልጠበቀው ምክር ተለግሶት ግራ ተጋብቷል:: እራሱ የሚያምናቸው ከፍተኛ የህግ አማካሪዎቹ በማያሻማ ቋንቋ ፍርድቤቱ የቅንጅት መሪዎችንና ሌሎችንም የህሊና እስረኞች በነጻ ከመልቀቅ በስተቀር ሌላ ምንም አይነት ብይን የሚያሰጥ የህግ መሰረትና የመረጃ ብቃት የሌለው መሆኑን ባለፉት ሳምንታት ግልጽ አድርገውለታል:: አስተሳሰቤንና አመለካከቴን ይጋራሉ የሚላቸው ከፍተኛ የህግ አማካሪዎቹ እንዲህ አይነቱን አስተያየት ይሰነዝራሉ ብሎ ያልጠበቀው ወያኔ በህግ አይን ሊያስቀጣ የሚችል የፈጠራ ወንጀል እስከሚያደራጅ ድረስ መጪውን የፍርድ ብይን በቀነ ቀጠሮ እንዲያስተላልፍ ለቃሊቲ ችሎት ትእዛዝ ሰጥቷል::

የህግ አማካሪዎቹ አስተያየት ያሳሰበው ወያኔ/ኢህአዴግ መላ ሲመታ ከከረመ በኋላ ሰሞኑን በብሄራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት እና በፌዴራል ፖሊስ ጸረ- ሽብር ሃይል ስም የቅንጅትን መሪዎች ከሽብርተኛነት ጋር የሚያቆራኝ፣ በራሱ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ፣ በካድሬ በረከት ስምኦን የተጻፈ መግለጫ አውጥቷል:: ከእዚህ መግለጫ ጋር ተያይዞ በሃሰት ምስክርና መረጃ የተደገፈ ሌላ ክስ ለማቅረብ የሚያስችለው ዝግጅት ቀጥሏል:: ይህንን ክስ ለማደራጀት የተመለመሉ ጠበቆች በጠቅላይ ሚኒስትሩ የበላይ ተቆጣጣሪነት ስራቸውን ከጀመሩ አስር ቀናት አልፏቸዋል:: እየተሸረበ ያለው የሃሰት ክስና መረጃ በሚገባ እስከሚጠናቀቅና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ሌላ ተለዋጭ መመሪያ እስከሚሰጠው ድረስ በቅንጀት መሪዎችና በሌሎች የህሊና እስረኞች ላይ ብይን ያስተላልፋል ተብሎ የሚጠበቀው ፍርድ ቤት ጉዳዩን በተከታታይ የቀን ቀጠሮዎች እንዲያጓትተው መመሪያ ደርሶታል::

ሰኞ የካቲት 26 1999 የሚያስችለው ችሎት በፖለቲካ ጌቶቹ ስለታዘዘ ውሳኔ አይሰጥም:: ይህ ብቻ ሳይሆን ይህን እያደረገ ያለው መለስ ዜናዊና ባልደረቦቹ ለሚያዘጋጁት የሃሰት ክስ ግዜ ለመስጠት ሲባል ነው:: ይህንን ስንገነዘብ እውን በታሪካችን ፍትህ እንዲህ በስሙ የተነገደበት ዘመን ይኖር ይሆን? እውንስ በታሪካችን በእዚህ ደረጃ ፍትህን ያራከሱ ዳኞች ታይተው ይሆን? የሚል ጥያቄ እንድናነሳ ያስገድደናል:: አምባገነንነት በሰፈነባቸው ስርአቶች በሙሉ የመጀመሪያው ሰለባ ከሚሆኑት ተቋማት አንዱ የፍትህ ተቋም ነው:: ፍትህን በሚመለከት የሃገራችን እውነታ የሚያሳየው ወያኔ የቀረቡለትን የሰላምና የእርቅ አማራጮች ሳይሆን በእብሪት የተሞላ አምባገነናዊ ህልሙን ለማሳካት ቆርጦ መነሳቱን ነው:: ይህ አካሄድ በሃገራችንና በህዝቧ ላይ ያጠላውን የግፍ ጥላ ግዝፈት ያረጋግጥልናል:: ፍትህን በሀገራችን ለማስፈን የምናደርገው ትግል ረጅምና መራራ መሆኑን ያሳየናል::

የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም አይነት ነጻነት ከሌለው ፍርድ ቤት ፍትሃዊ ውሳኔ ከመጠበቅ ይልቅ የወያኔን አምባገነኖች በተባበረና በጥንቃቄ በሚመራ የህዝባዊ እምቢተኛነት ትግል ወደ ህሊናቸው እንዲመለሱ ፣ አሻፈረኝ ካሉም በታሪክ እንደታዩት በርካታ አምባገነን ወንድሞቻቸው እጣቸው ከታሪቅ ቆሻሻ ላይ መጣል እንዲሆን ለእልህ አስጨራሹ ትግል ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል:: የወያኔ/ኢህአዴግም መሪዎች በግዚያዊ እብሪት ተደፋፍረው ሰብአዊ መብትን እየረገጡና ፍትህን እየፈነገጡ፣ እንዲህ አይነቱን ሃላፊነት የጎደለው እኩይ ድርጊት እየፈጸሙ ለዘላለሙ የኢትዮጵያን ህዝብ እየቀጠቀጡ መግዛት እንችላለን የሚል ህልም ካላቸው ዛሬም በቅንጅታዊው ሰብአዊ ፍቅራችን ይህ ህልም ወደ አስፈሪ ቅዠት ከመቀየሩ በፊት በፍጥነት ደግመው ደጋግመው አቋማቸውን እንዲያስቡበት ጥሪያችንን እናቀርባለን::

**የህግ የበላይነት የሰፈነባት ኢትየጵያን ለመገንባት ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ!!**

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ**
**አለማቀፍ የፖለቲካ ኮሚቴ**



Kinijit International Political Leadership Secretariat, P.O.Box 14701 Silver Spring MD, 20911 USA
Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974 www.kinijitethiopia.org